Co-funded by the European Union

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Better Migration Management
Horn of Africa



# በአፍሪካ ቀንድ የተሻለ የፍልሰት አስተዳደር ፕሮግራም (ቢ.ኤም.ኤም)

## ጠቅላላ ይዘት

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያሉ ሀገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ቤታቸውን ለቀው ከክልሉ ለሚመጡ ሰዎች እንደዋነኛ የስደተኞች መነሻ፣ መተላለፊያ እና መድረሻዎች ናቸው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን የስደተኞችን፣ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ፣ ፍልሰተኞችን እና በሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ቁጥር ወደ 15 ሚሊዮን ገደማ እንደሚገመት ሲገልፅ ከእነዚህ ውስጥ 5.7 ሚሊዮን የሚሆኑት ፍልሰተኞች ናቸው (ተመድ, 2011)፡፡ እንደ ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) መረጃ ከሆነ 51 ከመቶ የሚሆኑት በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሲሆን በምሥራቅ መንገድ በኩል ወደ ባሕረ-ሰላጤ አገሮች የሚጓዙት በ36 በመቶ ይከተሏቸዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ በደቡብ በኩል ወደ ደቡብ አፍሪካ ወይም በሰሜናዊው መንገድ ወደ ማግሬብ ክልል እና አውሮፓ የሚወስደውን  መስመርን ይጠቀማሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ብዙዎቹ ከችግር የተነሳ ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ይጓዛሉ፣ ማለትም ያለ ቪዛ ወይም ያለ ህጋዊ ወረቀት። አብዛኛውን ጊዜ ጉዟቸውን እንዲያመቻቹላው ራሳቸውን ለከባድ አደጋ ያጋልጣሉ በማጋለጥ የኮንትሮባንዲስቶችን ድጋፍ ይጠይቃሉ፡፡ ተጋላጭነታቸው የወንጀል መረቦችን እና የሰው ልጆችን ለትርፍ የሚበዘበዙ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ቀላል ዒላማ ያደርጋቸዋል፡፡ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የ150 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ኢንዱስትሪ ነው ተብሎ የሚገመት ሲሆን በ 21ኛው ክፍለ ዘመን እጅግ በፍጥነት

Better Migration Management
Horn of Africa

| | |
|---|---|
| **Project name** | Better Migration Management programme |
| **Partner Countries** | Djibouti, Ethiopia, Eritrea, Kenya, Somalia, South Sudan, Sudan, and Uganda |
| **Volume** | EUR 81 mio. (EUR 70 mio. EUTF/EUR 11 mio. BMZ) |
| **Duration** | April 2016 to September 2022 |
| **Implementing Partners** | British Council, CIVIPOL, Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH, International Organization for Migration (IOM), United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC). Expertise France and the Italian Department of Public Security were also implementing partners in phase I. GIZ heads the implementing partnership. |

በማደግ ላይ ከሚገኙት ድንበር ተሻጋሪ የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ነው (የዓለም የስራ ድርጅት፣ 2010)፡፡

ፍልሰት ብዙ ዘመናትን የቆየ ዓለም አቀፍ ክስተት ነው፣ ነገር ግን ፍልሰትን የሚደግፉ ፖሊሲዎች ፣ ህጎች ፣ መሰረተ ልማት ፣ የቀጠና

Implemented by

giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH · BRITISH COUNCIL · CIVIPOL CONSEIL · IOM UN MIGRATION · UNODC United Nations Office on Drugs and Crime

እና የድንበር ተሻጋሪ ትብብር እና እውቀት አለመኖር ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላል እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ለሆኑ እና ተጋላጭ ለሆኑት ስደተኞች አስፈላጊውን ድጋፍና ጥበቃ ለማድረግ በድጋፍ ሰጪ ሀገሮች ደህንነትን እና ህጋዊ ፍልሰትን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶችን ማደናቀፉን ቀጥሏል፡፡

## የተሻሻለ የፍልሰት አስተዳደር አካሄድ እና ተግባራት

የፕሮግራሙ አጠቃላይ ዓላማ የአገራት ባለሥልጣን መስሪ ቤቶች ተቋማት ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ ሕጋዊ እና  መደበኛ ፍልሰትን እንዲያመቻቹ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ እና ወደ ውጭ ለሚደረጉ የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውሮች የሰብዓዊ መብቶች ተኮር አሰራርን በመተግበር በተገቢው ምላሽ መስጠት እና መቀነስ እንዲችሉ ማድረግ ነው ፡፡ እንቅስቃሴዎች በሶስት ተያያዥነት ባላቸው አካላት - የፍልሰት አስተዳደር ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ማሻገርን ለማቆም ውጤታማ ተቋማት መፍጠር እና ለአደጋ ተጋላጭ ስደተኞች ጥበቃ መስጠት አማካኝነት ይተገበራሉ፡፡ በፕሮግራሙ ምዕራፍ I ውጤት ላይ የሚመርኮዘው ሁለተኛው ምዕራፍ የሚያተኩረው ፍልሰት አስተዳደርን በክልላዊ ፣ ሁሉን አቀፍ በሆነ አቀራረብ ማጠናከር እና ከፕሮግራሙ ቆይታ በላይ ዘላቂነቱን በማረጋገጥ ላይ ነው፡፡

## የፍልሰት አስተዳደር

ቢ.ኤም.ኤም ከምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና ከአፍሪካ ህብረት (አ.ሕ) ጋር በትብብር የተቀናጀ የቀጠናው የፍልሰት አስተዳደር ላይ የራሱን አስተዋፅዖ ያደርጋል ፡፡ የአገራት መንግስታት ፍልሰትን ለማስተዳደር እንዲችሉ የብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲዎችን እና ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እና በማሻሻል ድጋፍ ደርጋል፡፡ ፕሮግራሙ በናይሮቢ ውስጥ በ 2019 የተቋቋመውን የኬንያ የስደተኞች ጥናት ተቋም በክልሉ ውስጥ ካሉ ፍልሰተ-ነክ የመንግስት የባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ላይ በማነጣጠር የቀጠናው  የፍልሰት ጥናት ልህቀት ማዕከል ሆኖ ድጋፍ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ ከ27 አባል አገራት የመጡ የስደት ባለሙያ መኮንኖች የመጀመሪያውን የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን እ.ኤ.አ. በግንቦት 2012 ያጠናቀቁ ሲሆን ሁለተኛው ትምህርት ደግሞ በመስከረም 2013 ተጀምሯል፡፡



እንደ ኢትዮጵያ እና ሱዳን ያሉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች ወቅታዊ ፍልሰተኛ ሠራተኞችን ሁኔታ ሕጋዊ ለማድረግ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ©GIZ/Wasil Engel

ፕሮግራሙ በጋራ የመፍትሄ ሃሳቦችን ፣ አወቃቀሮችን እና አሰራሮችን በማዘጋጀት ለምሳሌ ህጋዊ እና ጥበቃ የሚደረግለት የጉልበት ወደ ሱዳን የሚገቡ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ፍልሰትን እንዲሁም የሱማሌ-ጅቡቲ የድንበር አስተዳደር አሰራሮችን እንዲሁም ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያበረታታል፡፡ ከልምድ እንደታየው የድንበር ተሻጋሪ ማዕቀፎች ያስለፈልጋሉ፣ የዝግጅቱ አላማ ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን (አ.ሕ) ከምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና ከምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ (EAC) ጋር በመተባበር የሁለትዮሽ የስራ ስምምነቶች ሞዴል ማዘጋጀት ነው፡፡



እንደ ፀረ-ሕገ-ወጥ ንግድ ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተካሄዱት ክልላዊ ኮንፈረንሶች በአገሮቹ መካከል ያለውን ትብብር አጠናክረዋል ፡፡ ©GIZ/Sari Omer

ቢ.ኤም.ኤም በብሔራዊ እና በቀጠና ደረጃ ፍልሰትን በማስተዳደር ዙሪያ ተቋማትን በመደገፍ ብሔራዊ መንግሥታትን ያጠናክራል፡፡ እነዚህ ብሔራዊ የማስተባበር ዘዴዎች (NCMs) ሁሉንም የሚመለከታቸውን ሚኒስትሮች (የፍትህ፣ የአገር ውስጥ ጉዳዮች፣ ጤና፣ ትምህርት፣ የሠራተኛና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወዘተ)፣ ሲቪል ማኅበራት እና የአካባቢውን ማህበረሰቦች ተወካዮችን ያካተቱ ግብረ ኃይሎች ናቸው፡፡ በሀገር አቀፍ እና በክልሎች ደረጃ ተገቢ እርምጃዎችን ለማዘጋጀት፣ ለመገምገም እና ለማስተባበር እንዲቻል ግብረ-ኃይሉ ከስደት ጋር የተያያዙ ሁሉንም ጥያቄዎች ይመለከታል፡፡ የብሔራዊ የማስተባበሪ ዘዴዎች በተለያዩ የመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተዋንያን መካከል የሚኖር ትብብርን ያሳድጋሉ፣ ይህ የሕግ የበላይት ተቋማትን በተሳካ ሁኔታ ለማሻሻል፣ በሰው ልጆች ላይ የሚደረግ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመቋቋም እና ለአደጋ ተጋላጭ ስደተኞች የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ዘላቂ ጥበቃ እና ድጋፍ ሰጪ መዋቅሮች ለመፍጠር የሚያስችላቸው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ብሔራዊ የማስተባበር ዘዴዎች ከኡጋንዳ በስተቀር በሁሉም የፕሮጀክቱ ምዕራፍ I ውስጥ የተመሰረቱ ወይም እንደገና የተካተቱ ሲሆን አሁን ባለው ምዕራፍ II እድገታቸው ይጠናቀቃል፡፡ ፕሮግራሙ የእነዚህን የብሔራዊ የማስተባበር ዘዴዎች የድርጊት መርሃ ግብሮች እና ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት፣ የፍልሰት አዝማሚያዎችን እና አስፈላጊ ምላሾችን ለመተንተን እንዲሁም የስልጠና ፍላጎቶችን ለመለየት (እና ምላሽ ለመስጠት) እንዲቻል መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያግዛል፡፡

ፕሮግራሙ ከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ አገራዊ ህጎችን እና ፍልሰትን በተመለከተ ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ረገድም መንግስታትን ያግዛል፡፡ በተለይም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ በማዘዋወር ላይ ሕግ በማውጣ፣ እንዲሁም በውጭ አገር የሥራ

ምልመላ ዘርፍ በተለይም በኢትዮጵያ እና በኡጋንዳ ቁጥጥር እን ዲደረግ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የመጨረሻው ኩባንያ ኩባንያዎች በውጭ አገር በተለይም በባህረ ሰላጤው ሀገሮች ውስጥ በአስቸ ጋሪ በሆኑ እና ከዚያም አልፎ ብዝበዛ በሚያስከትሉ ሥራዎች ላይ ሰዎችን እንዳይቀጥሩ ለመከላከል የታቀደ ነው ፡፡ የኡጋንዳ የውጭ አገር ሥራ ምልመላ ኤጀንሲዎች ማህበር እንዳስታወ ቀው 140,000 የሚሆኑ ኡጋንዳውያን በመካከለኛው ምስራቅ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች አማካኝ ነት ሊከተል የሚችለውን በደል ሊያበረታቱ በሚችሉ ግልጽ ባልሆኑ የውል ሁኔታዎች ውስጥ የሚመለመሉ ሲሆን አብዛኛ ውን ጊዜ ያለፍላጎታቸው ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ ፡፡



መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያን ከስደተኞች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በአውደ ጥናቶች እና ስልጠናዎች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ ©GIZ

## ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ማሻገርን ለመቅረፍ የሚሰሩ ውጤታማ ተቋማት

ቢ.ኤም.ኤም የፍልሰት ፖሊሲዎችን እና ህግን ተግባራዊ የሚ ያደርጉ ተቋማትን ውጤታማነት ያሻሽላል፡፡ ፕሮግራሙ አሁን ያሉትን የቀጣናውን ተነሳሽነት በማቀናጀት እና በዓለም አቀፍ ግዴታዎች እና መስፈርቶች መሠረት በሕግ አስፈፃሚዎች፣ በፍ ትህ አካላት እና በሌሎች የመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተዋንያን መካከል ያለውን የብሔራዊና ድንበር ተሻጋሪ ትብብር ጥራት ለማሳደግ ያለመ ነው ፡፡ ይህ ለዩኒቨርሲቲዎች እና ለሌ ሎች የህግ ማስከበር ስልጠና ተቋማት ሥርዓተ-ትምህርትን ማዘ ጋጀትና መተግበር፣ የሥልጠና ቁሳቁስ ማምረት እና የሕግ አስከ ባሪ ኤጀንሲዎች የሥልጠና ኮርሶችን መቅረጽ እንዲሁም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ማሻገር ጉዳዮች ላይ የምርመራ ጥራ ትን ማሻሻል እና በህግ መጠየቅን ያካትታል፡፡ በፖሊስ እና በአ ቃቤ ህግ አገልግሎቶች መካከል ትብብርን ለማሳደግ መደበኛ አሰራሮች ይቋቋማሉ ወይም ያጸድቃሉ፡፡

ፕሮግሙ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን እና ተጋላጮችን እና ድንበር ተሻጋሪ ፍልሰተኞችን ለመለየት እና አግባብ ወዳ ለው የጥበቃ እና የእርዳታ አገልግሎቶች ለመላክ ከፖሊስ፣ ከሲ ቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከድንበር ባለሥልጣናት እና ከኢ ሚግሬሽን አገልግሎቶች የመጀመሪያ የተወጣጡ ምላሽ ሰጭዎ ችን አቅም ያሳድጋል፡፡ ይህ በመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ ሰጪዎች እና በመንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ አገልግሎት ሰጭ ዎች መካከል (እንደ ማህበራዊ ሰራተኞች፣ የልጆች ጥበቃ ሀላፊ ዎች፣ ለሴቶች ደህንነት ጥበቃዎች ፣ ወዘተ) የተጠቂዎችን ደህን ነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ከምርመራው የመጀመሪያ ደረጃ ዎች አንስቶ እስከ መጨረሻው የፍርድ ሂደት ድረስ ያለውን ቅን ጅት ያስተባብራል፡፡ ቢ.ኤም.ኤም የፍልሰት ሰብአዊ አገልግሎት አስተዳደርን ለማበረታታት እና በክልላቸው ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት በሚመለከታቸው የመንግስት እና መንግስታዊ ባል ሆኑ ተቋማት መካከል የድንበር ተሻጋሪ ማስተባበሪያ አካላትን፣ ቡድኖችን እና ተነሳሽነቶችን ይደግፋል፣ ለምሳሌ በተዘጉ ድንበ ሮች ስደተኞችን አልፈው እንዲወጡ ሲያደርጉ፡፡

በተጨማሪም የብኤምኤም የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ወይም ሌሎች የሕገ ወጥ ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ እና ተጋላጭ የስ ደተኞችን ብዝበዛ የመከታተል, ሪፖርት የማድረግ እና ምላሽ የመስጠት ተልዕኳቸውን እንዲወጡ በብሔራዊ የሰብአዊ መብ ቶች ተቋማት እና በሌሎችም ስልጣን ያላቸው ድንበት ተሻጋሪ ተቋማት አካላት ውስጥ ያሉ ተቆጣጣሪ አካላት ይደግፋል፡፡ የሰ ብአዊ መብት ተቋማት አባላት በስደተኞች መብቶች እና የሰብ አዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ በሴቶች፣ ወንድ እና ልጃገረ ዶች ላይ ያተኮሩ የቅሬታ ስልቶችን ይቀበላሉ ፡፡

የቢ.ኤም.ኤም የቀጠና እና የሰብአዊ መብት ተኮር አሰራር ለአፍ ሪካ ቀንድ የተዘጋጀ የብሔራዊ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች መድረክን ድጋፍ ለመስጠት የተያዙ እቅዶችን ያካትታል፡፡ ፕሮግራሙ በስ ደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ድንበር ተሻጋሪ የሰብአዊ መብት ጥሰ ቶች ዙሪያ ቁጥጥርን፣ ሪፖርት ማድረግን፣ መረጃን ማጋራትን እና ጣልቃ ገብ ስልቶችን ለማዘጋጀት ትብብሮችን ያጠናክራል፡ ፡ መደበኛ የሆነ ውይይት በስደተኞች ላይ ስለሚፈፀሙ የሰብ አዊ መብት ጥሰቶች ምንነት ግንዛቤን ያሳድጋል እንዲሁም በክ ልል ደረጃ ፍልሰትን እና የሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ ጉዳ ዮችን በመፍታት ዘላቂ የሆነ ጣልቃ ገብነትን ለመፍጠር ያለውን ትብብርን ያሻሽላል፡፡

## ጥበቃ

ቢ.ኤም.ኤም ለህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ለሆኑ እና ለአ ደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ስደተኞች በአካባቢያዊ ፣ በአገራዊ እና በክ ልል ደረጃ ያለውን ድጋፍ እና ጥበቃን ያሻሽላ፡፡ ፕሮግራሙ ከአ ጋር አገራት የመጡ ወደ 60 የሚጠጉ የሲቪል ማህበራትን ያካ ተተ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ፍትሃዊ ፍልሰትን ለማሳደግ የቀጠ ናወን የሲቪል ማህበራት መድረክ መደገፉን ይቀጥላል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች መረቦች ድጋፍ የሚደረግላቸው በመካከላቸው ትብብርን ለመጨመር እና የማ ስተላለፍ ዘዴዎች ላይ ያላቸውን ሚና ለማጠናከር ዓላማ ነው፡፡

ፕሮግራሙ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ለሆኑ እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑት ስደተኞች ወደ ጥበቃ ስፍራዎች እና አገልግ ሎቶች መተላለፍ የሚችሉበትን ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ የመ ንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያን፣ የህግ አስከባሪ ኤጀ ንሲዎች፣ አገልግሎት ሰጭዎች እና ሲቪል ማህበራት ያሉበት አውታረ-መረብን ለማቋቋም እገዛ ያደርጋል፡፡ ቢ.ኤም.ኤም ስደ ተኞች ማስተላለፊ ላይ የሚመለከታውን ተዋንያን ያሰለጥናል እንዲሁም መደበኛ አሠራሮችን በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድ ረግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ሥልጠና እና መሣሪያዎችን ያቀርባል ፣

እንደ የህክምና እና የስነ-ልቦና እንክብካቤ፣ የህፃናት ጥበቃ እና
መጠለያ ያሉ የአገልግሎት አቅርቦቶችን እና አቅሞችን ያሳድጋል።

በተጨማሪም ፕሮግራሙ በክልሉ በሚገኙ ልዩ እና አጣዳፊ የጥ
በቃ እና የድጋፍ ክፍተቶች ላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች
እና ለአገልግሎት ሰጭዎች ለቀጠናው እና ለብሔራዊ ፖሊሲ
አውጭዎች ግብረ-መልስ መስጠት የሚችሉበትን ስልታዊ ዘዴዎ
ችን በማስተዋወቅ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በክፍል I፣ ፕሮግራሙ በመላ ኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በሶማሌላንድ፣
በሱዳን እና በጅቡቲ አገልግሎቶችን ለሚሰጡት ከ 300 በላይ
አቅራቢዎች ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች እና ተጋላጭ
ፍልሰተኞች የአገልግሎት አቅርቦቶችን በመለየት አጣርቶት ተረ
ጋግጧል ፡፡ በክፍል II ይህ መረጃ በማስተላለፍ ስርዓት ውስጥ
ያሉ ተዋንያን እና አገልግሎት ሰጭዎች ተገቢ አገልግሎቶችን ለማ
ግኘት የሚጠቀሙበትን የበይነ መረብ መድረክ ይፈጥራል፡፡ ቢ.
ኤም.ኤም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ለሆኑ፣ ተጋላጭ
ለሆኑ ፍልሰተኞች እና ወደፊት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ስደተኞች በአ
ገልግሎቶች እና በሕጋዊ ፍልሰት ላይ ያሉ መረጃዎች ለማሳደግ
ያለመ ነው ፡፡ ፕሮግራሙ ማህበረሰቦች፣ መንግስታት እና መንግ
ስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት በተለይ በሴቶች፣ ወጣቶች እና
በሴት ልጆች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ የፍልሰተኞችን ፍላጎትና
ምኞት የሚገልጹ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን ለማዘጋጀት ይረ
ዳቸዋል ፡፡

ቢ.ኤም.ኤም እንዲሁ በተቀባይ ሀገሮች ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር
ሰለባ ለሆኑ እና ተጋላጭ ለሆኑ ስደተኞች ዘላቂ መፍትሄዎችን
ለመስጠት ያለመ ነው፡፡ ይህ ወደ አገራቸው የመመለስ ተስፋ በሌ
ላቸው እና በተጠበቁ ቤቶች ወይም በሌሎች መጠለያዎች ውስጥ
ሊቀሩ የሚችሉትን ስደተኞችን ይመለከታል፡፡ ፕሮግራሙ የሕል
ውና አማራጮችን ለመለየት የሚመለከታቸው የግል፣ የመንግስት
እና የሲቪል ማህበረሰብ ተዋንያንን በማህበረሰብ ደረጃ በበርካታ
ባለድርሻ ውይይቶች ላይ ያሳትፋል ፡፡ ይህ በሌሎች የአውሮፓ
ህብረት እና በሁለትዮሽ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ አካላት የሚሰጣቸ
ውን የህልውና ፕሮግራሞች እንዲሁም ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ተነሳ
ሽነቶችን ያጠቃልላል፡፡

## የቢ.ኤም.ኤም ውጤቶች (ኤፕሪል 2016 - መስከረም 2020)

16,800 የአገራት የስራ ክፍሎች የፍልሰትን የተቀናጀ አስተዳደር
ለማሻሻል እና ብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲዎችን ፣ ህጎችን እና
ድንበር ተሻጋሪ ትብብርን ለማጠናከር ድጋፍ አድርገዋል፡፡

በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምርመራ እና ክስ፣ የተቀናጀ
የድንበር አስተዳደር እና ስደተኞችን ወደ አገልግሎት
በማስተላለፍ መስክ ለ 5,470 የክልል እና መንግስታዊ ላልሆኑ
ተዋንያን 242 የአቅም ግንባታ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

4,020 መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተወካዮች
አገልግሎቶችን በማሻሻል እና ለአደጋ ተጋላጭ ስደተኞች እና
ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን የመረጃ ተደራሽነት
ለማሻሻል በተከናወኑ ተግባራት ላይ ተሳትፈዋል፡፡

በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና የስደተኞች መብቶች ዙሪያ
በሕዝብ ግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎች 16.2 ሚሊዮን ሰዎች
ተሳትፈዋል፡፡

18,200 ተጋላጭ ስደተኞች በመጠለያ ፣ በመሰረታዊ
አገልግሎቶች ፣ በሕክምና ድጋፍ ታግዘዋል (ምዕራፍ 1 ብቻ) ፡፡

## መግቢያ

በአፍሪካ የካርቱም የውይይት ሂደት ለተቀመጡት ፍላጎቶች
ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል የአውሮፓ ህብረት እና ጀርመን
በ2016 BMMን አቋቋሙ፡፡ ሂደቱ በሰፊው አፍሪካ ቀንድ ላይ በአ
ውሮፓ ህብረት፣ በመነሻ፣ በመተላለፊያ እና በመድረሻ በአባል አገ
ራት መካከል የሚደረግ የቀጠናው የምክክር እና የትብብር ሂደት
ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ፍልሰተኞ
ችን በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር ነው ፡፡ የቢ.ኤም.ኤም ተግባ
ራት ከአፍሪካ ህብረት እና ኢጋድ ጋር በመቀናጀት፣ እንደ ዘላቂ
የልማት ግቦች፣ ዓለም አቀፍ ደህንነቱ የተጠበቀ ሥርዓትን የተከ
ተለ እና መደበኛ ፍልሰት ጥምረት፣ የአፍሪካ ህብረት የፍልሰት
ፖሊሲ ማዕቀፍ እና የኢጋድ የክልል ፍልሰት ፖሊሲ ማዕቀፍ ያሉ
ዓለም አቀፋዊ እና ቀጠናዊ ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ ይተገ
በራሉ፡፡ በተጨማሪም ቢ.ኤም.ኤም ከሌሎች የአውሮፓ ህብረት
እና በሁለትዮሽ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ፕሮጀክቶች እና ተነሳሽነ
ቶች ጋር ለመገናኘት ከክልላዊ እና ብሄራዊ አጋሮች ጋር በቅርብ
በመተባበር ይሰራል፡፡

**Published by** Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

**Registered offices** Bonn and Eschborn, Germany

**Project** Better Migration Management Programme
Rue de la Charité 33 / Liefdadigheidsstraat 33
1210 Bruxelles/Brussels
Belgique/België

**Contact** Sabine Wenz, Programme Director
E-mail: sabine.wenz@giz.de
Phase II EUTF website
Phase I EUTF
GIZ website

**Design/Layout** GIZ/Ira Olaleye

**Photo credits** GIZ

The programme is co-funded by the European Union and the German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development (BMZ).

GIZ is responsible for the content of this publication.

**As at** September 2020, Brussels